የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪<br>አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፱ | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 13th Year No 32<br>ADDIS ABABA 7th June, 2007 |
|---|---|---|

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፱/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ለሁለተኛው የገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስ ፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተ ፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ገጽ ፫ሺ፮፻፲፭

Proclamation No. 529/2007

African Development Fund Loan Agreement for Rural Electrification Project II Ratification Proclamation Page 3615

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፱/፲፱፻፺፱

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሁለተኛ የገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮጀክት ከፊል ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፹፯ ሚሊዮን ፪ መቶ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት /ሰማንያ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት/ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፲፪ ቀን ፪ሺ፯ በቱኒዝ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው የገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፱/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 529/2007.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS**, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding UA 87,200,000 (eighty seven million two hundred thousand Units of Account) for financing Rural Electrification Project II, was signed in Tunis on the 12th day of January 2007;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 17th day of May, 2007;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Rural Electrification Project II Ratification Proclamation No. 529/2007."

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፲፪ ቀን ፪ሺ፯ በቱኒዝ የተፈረመው ቁጥር 2100150013644 የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፹፯ ሚሊዮን ፪ መቶ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት /ሰማንያ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No. 2100150013644 signed in Tunis on the 12th day of January 2007 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is ratified.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is here empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of UA 87,200,000 (eighty seven million two hundred thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of June, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት